# በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሠላም ለማስፈን የኤርትራ፣ ሶማልያ፣ ኢትዮጵያ ወጣቶች ትብብር

ከበየነ ከበደ

ፖለቲካ ሁሉንም መልካም አማራጮች ሥራ ላይ የማዋል ክህሎት ነች (art of the possible)። እኔ ከዚህ በታች ያለውን የምጽፈው የዛሬውንነባራዊ እውነታ (objective reality) ተመርኩዤ ነው። ነገ ሊከሰት የሚችለውን ሁኔታ አላውቀውም። ከምዕራብያውያኑና መከከለኛው ምሥራቅ ሃገሮች ጣልቃ ገብነት ጋር ተዳምሮ ድርቅ፣ በሽታ፣ እርዛት፣ ድህነት፣ ጦርነት፣ የሚያምሰውን የአፍሪካ ቀንድ ሕዝብ ማንም አላሰበለትም። የመንግሥት ለውጥ፣ አብዮት፣ የመገንጠልና መስፋፋት ጦርነት፣ ወዘተ፣ አንዳቸውም ለዚህ ሕዝብ አልበጁም። ያለፈው አለፈ ዛሬስ? የኤርትራ፣ ሶማልያ፣ ኢትዮጵያ ወጣቶች መልካም ትብብር ፈጥረው ቢራመዱ በአፍሪካ ቀንድ ላይ የሚሰቃዩትን ምስኪን ነዋሪዎች እንባ ያብሳሉ" የሚል እምነት አለኝ።

የአፍሪካ ቀንድ

ቅኝ ገዥዎች የተቀራመቷት መላ አፍሪካ በእጅ አዙሩ ብዝበዛ ስትማቅቅ የአፍሪካ ቀንድ ተጨማሪ መከራ ታስተናግዳለች። መሪዎች በየሃገራቸው ያለውን አመጽና ተቃውሞ ለማብረድ ወይም ከጎረቤት ሃገር የሚሠነዘርባቸውን ጥቃት ለመከላከል ከአሜሪካ ወይም ሶቭየት ሕብረት ጋር ሲወግኑ የአፍሪካ ቀንድ የሁለት ርዕዮተ ዓለሞች መቆራቆሻ ምድር ሆነች። ኃያላኖቹ መሬቱን የጦር መሳርያዎቻቸው መሞከርያ ሲያደርጉት ነዋሪው ቀዬውን እየለቀቀ ተሰደደ። ዛሬም ቢሆን በልማት ስም ቀጠናውን በተቆጣጠረችው ቻይናና አሜሪካ መካከል ያለው ሽኩቻ ሄዶ ሄዶ የት እንደሚደርስ መገመቱ አያስቸግርም። ሩስያ፣ ቻይናና አሜሪካ ብቻ አይደሉም ስትራቴጅያዊ ዓላማቸውን እውን ለማድረግ ቀልባቸውን አፍሪካ ቀንድ ላይ የሚጥሉት - የተባበሩት የዓረብ ኤሚሬትስ፣ ቱርክ፣ የገልፍ ሃገሮች፣ ኢራን፣ እስራኤልም ጭምር ናቸው በትርምሱ ዙርያ አንዣበው ፍላጎታቸውን የሚያሳኩበትን ፖሊሲ የሚቀርጹት።

ጠንካራ ተቋማት መገንባት ያልቻሉት የአፍሪካ ቀንድ ሃገሮች ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅቶች አሏቸው። መንግሥታቸውን በአመጽ ለመጣል ወጥነው ጽኑ ተፋላሚዎችን ያሰለጠኑት እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች እርዳታ ለማግነት አንዱ ስልታቸው የኃያላን አገሮችን ወይንም የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችን ትኩረት ሳቢ (pull factor) መሆን ነው። ሁሉም ለሥልጣን ነው የሚዋጉት። ኤርትራ የተገነጠለችው ከብዙ ደም ግብር በኋላ ነው። ዘራፊዋ ሕወሃት በዋዛ አይደለም ሥልጣን ኮርቻ ላይ የተፈኛጠጠችው፤ ትግራይዋውን ገብራ ነው። ሱዳን ሁለት እስክትሆን የደሆች ደም ፈሷል። በሶማልያ የጎሳ መሪዎች እርስ በእርስ ተከፋፍለው ሶማልያን የምስኪኖች መቀበርያ አድርገዋታል። የአፍሪካ ቀንድ የብዙ ጎሳዎች መኖርያ ቤት ነች። ሁሉም ጉሳዎች የጦር ጀግኖች አሏቸው። በጦር ጀግኖቹ መካከል ሽኩቻ አለ። ያንደኛው ደጋፊ የዛኛውን ደጋፊ ይንቃል። ይኼኛው ከዚያኛ ጋር ወግኖ ያኛውን ያጠቃል። እብሪትና ማን አህሎኝነት የአፍሪካ ቀንዱ ፖለቲከኞች ልዩ መለያ በመሆኑ - ስለ ሠላም ማውራት፣ በጠረቤዛ ዙርያ መደራደርና መወያየት ተሸናፊነትና ተንበርካኪንት ነው።

ከላይ ባየናቸው ትዕይንቶች ምክንያት የአፍሪካ ቀንድ ጊዜአቸውን ጠብቀው በሚፈነዱ ፖለቲካዊ ገሞራዎች የሚንተከተኩባት ትኩስ የትርምስ ቀጠና ነች። ትርምሱ በጥቅማጥቅም ግጭትና ምክንያት በሌለው ንትርክና ብሽሽቅ የታጀቡ ናቸው። ግጭትና ንትርክ የሃሳብ ጠላቶች ናቸው። ፋታ ያላገኘች ኅሊና ምርምርም ሆነ አመክኗዊ ምክንያቶች መደርደር አትችልም። ምርምርና አመክኗዊነት የራቁት ህብረተሰብ ቢሠራም ለዕለት ጉርሱ፣ ቢጸልይም ለዕለት እንጀራው እንጂ የነፋስ ወፍጮ ለመትከልም ሆነ የጉድጓድ ውሃ ቆፍሮ ለማውጣት ብቃቱ አይኖረውም። ወገኖቼ! እስከመቼ በሚበሻሽቁ ፖለቲከኞች ክፉ ሃሳብ ተጠምደን እንገዳደል? እስከመቼ ዝናን ለሚቃርሙ ፖለቲከኞች ስንል ሃገር ጥለን እንሰደድ? እስከመቼ ዲቪ እንሙላ? እስከመቼ ትምህርት እየተውን የጥገኝነት ኬዝ እናጥና? እስከመቼ እንለምን? ዛሬ ቆመን ማሰብ አለብን።

## ስደት

በርካታ ኤርትራውያን፣ ኢትዮጵያውያንና ሶማሌያውያን ሃገራቸውን ለቀው ተሰደዋል። በአፍሪካ ቀንድ ላይ የሰፈነውን መከራ መሸከም ያልቻለው ሁሉ ይሰደዳል። ምሁሩ፣ ወጣቱ፣ ባለሙያው ቀጠናውን ለቆ ፈርጥጧል። የቀሩትም ቀጠናውን ለቀው እንዴት እንደሚወጡ ነጋ ጠባ ያስባሉ። ስደት ዋዛ አይደለም፣ የአውሬ ሲሳይ ያደርጋል። ሲሰደዱ እውቅያኖስ መስመጥም አለ። ሲሰደዱ የአካል ብልት እያወጡ በሚሸጡ አራጆች መከበብና መታረድ አለ። ሲሰደዱ አስኮብላዮች ጥቃት መዳረግም አለ። እግሩ ምዕራብያውኑ አገር ያደረሰው እድለኛ የራሱን መንግሥት ወንጅሎ ጥገኝነትን ሲጠይቅ፣ ያላደለው በየአረብ አገሮቹ ጉልበቱን ይሸጣል። ብዙዎች ለቀው ከወጡም በኋላ የሃገራቸውን ፖለቲካ በስሜት ስለሚከታተሉ ሳይማሩ ቀርተዋል። አንዳንዱ በከባድ ሥራ ተጠምዶ እድሜውን ይፈጃል። በርካታ ምሁር ምድሪቱን ለቆ ሲሄድ የምዕራብያውያኑ ብልሹ ባህልና ሙስና ይፈረጥማል። ልማትም ሥልጣኔም ያልሆነው ጎጂ ባህል ሥነ ምግባርን ንዶ ባለጌዎችን ሲያበዛ ስደትም ይበዛል።

## ሕወሃት

ዓላማዋን በማሳካት ረገድ ከኃያላኖቹም ሆነ መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ይልቅ የተዋጣላት ሕወሃት ነች። ሕወሃት እቀጠናው ላይ ነግሳ ለመቆየት ሶስት መሠረ አላማዎችን ሥራ ላይ አዋለች። ሀ. ድብቅ ፍላጎትን በሤራ ማሳካት፣ ለ. ዘረኝነትን ማባባስ፣ ሐ. "ራስን በራስ ማስተዳደር" ጽንሠ ሃሳብን አጣሞ ለራስ ዓላማ የማስፈጸም ስልትን መጠቀም ናቸው። እስቲ እንያቸው።

ሀ. ድብቅ ፍላጎትን ለማሳካት የሤራ ችሎታ – ሕወሃት የትግራይን ኃይማኖተኛ ሕዝብ አስቃቂ በሆነ ሁኔታ ከፈጀች በኃላ ሓውዜንን በቦምብ አስደብድባ ሳይወድ በግድ መከታና ጋሻዋ ያደረገችው። ሕወሃት የወደፊት ዓላማዬ እንቅፋት ናቸው ያለቻቸውን ኢዲዩንና ኢሕአፓን በጊዜ ነው ያስወገደቻቸው። ሕወሃት ስታማልለው የቆየችውን ኦነግ "ተገንጣይ" ነው ብላ መታችው። ሕወሃት "ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ወረረች" ብላ የወንድማማቾች ደም እንዲፈስ አደርጋ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ አባረረች። ሕወሃት ሽብርተኝነትን በመዋጋት ሰበብ ሶማልያ ገብታ የአሜሪካንን ድጋፍ ስታፈረጥም ኦብነግን በሽብርተኝነት አስፈርጃ ቀጠቀጠችው። ሕወሃት የሶማልያላንድንና የሶማሊያን ውጥረት ነግዳበት ነው መሪዋ መለስ ከአውሮፓ ሕብረት መሪዎች ጋር ፎቶ የተነሳው። ጥቅሟን ለማስጠበው ተወዳዳሪ የሌላት ሕወሃት በሶማልያ ክልል ሰውን ከአውሬ ጋር እንዲታሰር አድርጋለች። ሕወሃት "ተቃዋሚ" የምትላቸውን ሰዎች መጀመርያ የመሰደድ እድል ትሰጣቸዋለች፣ ያልተቀበሉትን በእስር ቤት በማሰቃየት ወይም አሸምቃ በመግደል ታስወግዳለች። በሕወሃት ዘመን የዘር ጥቃት ዒላማ የሆነው አማራ ገደል ተወረወረ፣ በገጀራና ሳንጃ ተሰቀሰቀ፣ እንዳይወልድ መከነ፣ ምድሩ እንዳያበቅል መርዝ ተርከፈከፈበት፣ በኦሮምያና ደቡብ ምድር ተገደለ፣ ተፈናቀለ፣። ሕወሃት አማራው ላይ የፈጸመችው መጠነ ሠፊ የዘር ማጽዳትና (ethnic cleansing) የዘር ግድያ (genocide) እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያፋፋመችው ጥቁር ሽብር (black terror)ለማዳፈን ደርግ ስለፈጸመው የስድሳዎቹ ባለሥልጣናት ርሸናና ቀይ ሽብር (red terror) ታወራለች። ሕወሃት ድብቅ ፍላጎቷን የምታሳካው በ"ህገ መንግሥቱ ይከበር" ልፈፋ፣ "በአንቀጽ 39" ማማለል፣ "በነፍጠኛ መጣብህ" ማስፈራራት፣ "በፌደራሊዝም፣ ልማትና ዴሞክራሲ" ጩኸት ነው።

ለ.. ዘረኝነት – ሕወሃት ሥልጣኗን ለመቶ ዓመት ለማደላደል የተጠቀመችው ትልቁ ሤራ ዘረኝነትን አንግሶ ከፋፍሎ በመግዛት ነው። ሕወሃት የሁሉም ዘር ጠላት አማራ ነው፣ አማራውን የበላይ ገዥ ያደረገው ሚኒልክ ነው፣ የሚል የሃሰት ትርክት ፈጥራ የሞኞቹን ልህቃን የአስተሳሰብ አቅጣጫ ጠመዘዘች። ሕወሃት ሁመራን፣ ወልቃይጥን፣ ጠገዴን፣ ጸለምት፣ ራያን መስረቋ ሳያንሳት አማራን መድረሽያ እንዲያጣ አደረገች። ሕወሃት ለአንዱ ጎሳ መሳርያ ለሌላኛው ጥይት በመስጠት የሶማልያን ሕዝብ ታናክሳለች። ሕወሃት አፋርና ኢሳን፣ አኙዋክና ኑዌርን አጋጭታ አስታራቂ መስላ ብቅ ትላለች።

ሐ. የራስን እድል በራስ መወሰን -(ራስ ገዝ - እራስን በራስ ማስተዳደር) - በርካታ የጎሳ መሪዎችና ፖለቲከኞች"የራስን እድል በራስ መወሰን" (self determination) - (ራስ ገዝ - እራስን በራስ ማስተዳደር)የምትለዋን ውብ ጽንሠ ሃሳብ ይወዷታል። ሲያቆላጽሷት ደስ ስለምትለው ሲጨብጧት ግን ስለምታቃጥለዋ "የራስን እድል በራስ መወሰን" ጽንሠ ሃሳብ መለስና ስብሃት የስታሊንን መጽሃፍ በድንግዝግዝ ተረድተው "ሥነ ልቦና" "ቋንቋ" "ባህል" እያሉ አደናገሩ። በራስ መወሰን ሁለት ነች። አንደኛዋ "ራስ" (self)ስትሆን ሁለተኛዋ ደግሞ "መወሰን" (determination) ነች። "ራስ" ተከፍላ ሁለት ስትሆን "መወሰንም" ሁለት ትሆናለች። "በራስ መወሰን" ባህሪይዋ እንደ አሜባ መባዛት ነው። ብዙ "ራሶችና" ብዙ "ወሳኞች" - በአጭር ቃል ብዙ ትርምሶች፣ ብዙ አለመግባባቶች፣ ብዙ ግጭቶች ናቸው። በብዙ "ራሶች" መካከል የሚደረገው የወሳኝነት ሽሚያ ነዋሪውን ለመከራ ሲዳርግ ሕወሃት ገደል እየጨመረችም ሆነ እልጇ ሬሳ ላይ እናትን አስቀምጣ እየገረፈች የዘረፋ ሥርዓቱን ታስቀጥላለች። "ከአህያ የዋለች ጊደር" እንዲሉ – ተረኞችም - "ራስን በራስ ማስተዳደር"፣ "የብሄር ብሄረሰብ ፖለቲካ"፣ "ክልል" - ለሚባሉት አማላይ ፖለቲካዎች የሚሰግዱት መሬት ወረራን፣ ህገ ወጥ ግንባታን፣ መሿሿምን እንደ ተቋም አስቀጥለው ለመዝረፍ ነው። ሙስና - ነገ ተነገ ወድያ - ተጠያቂ ማድረጓን የሚረዱት አስተውዮች ብቻ ናቸው ራሳቸውን የሚጠብቁት።

የሰማይ ስባሪ የሚያህል መከራ ያላጠፋት ኢትዮጵያ

ድህነት፣ እርዛት፣ ሰደት፣ ጦርነት የመሳሰሉት የአፍሪካ ቀንድ ሃገሮች ችግር እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ ከላይ ያየናቸው ሶስቱ ችግሮች ተጨመሩላት። ሕወሃት ከዓለም ባንክ በኢትዮጵያ ስም ከተገኘው ብድር ሞጭልፋ በተረፈው አስፋልት እያነጠፈች የድርብ አሃዝ እድገት ከበሮ ትመታለች። ሕወሃት የኢትዮጵያን ዓይኖች ጋርዳ ጎሳን ከጎሳ በማጋጨት፣ ልዩ ልዩ የሞት ድግሶችን እያዘጋጀች፣ አጸያፊ ባህሎች እንዲስፋፉ እያደረገች፣ መረጋጋት እንዳይኖር ሤራ እየጠነሰሰች ንብረትና ገንዘብ የመሰብሰብ ድብቅ ዓላማዋን አሳካች። ሃሰተኛ ነብይነት፣ ሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ፣ ሃሰተኛ የቦታ ካርታ፣ ሃሰተኛ መታወቅያ፣ ሃሰተኛ ገንዘብ - ሃሰተኞ ነገሮች ተጠቅለው የሕወሃት የሙስና ፈጠራዎች ናቸው። ብዙዎች መሬት እየወሰዱ ሲሸጡ ደሆች በጦርነት፣ ድርቅ፣ እርዛት፣ የዘር ግጭት፣ ዘርን ማጽዳት፣ ወዘተ፣ ምክንያት ይራባሉ፣ ይሰደዳሉ፣ ይሞታሉ። ሕወሃት በዚህ በኩል ቤተ ክርስትያን እንዲቃጠል እያዘዘች በዚያ በኩል ንብረት ታሸሻለች። ሕወሃት አማራውን ከትግራይዋው፣ ኦሮሞውን ከአማራና ሶማልያ፣ ደቡቡን እስር በእርስ በማጣላት – ውሑድ ማንነት የተላበሰውን ማኅበራዊ መሠረት አናግታ ፍቅርና አብሮነት አጠወለገች። ሕወሃት ሌብነትን አስፋፋታ "የራስን እድል በራስ መወሰን" ፖለቲካን እየተረከች የሃገር ኅልውና አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ አደረገች። ሕወሃት ሙሰኛ፣ ሥነ-ምግባር ጠል ብቻ አይደለችም። ሴሰኝነትና ብልግናም የሕወሃት የንዋይ ቁልል የወለዳቸው ነውሮች ናቸው። በሃገሪቱ ላይ በሠፊው የታየው የሕወሃት ልጆች ቅብጠት ከመጋረጃው ጀርባ ያለውን ቅጥ ያጣ ምዝበራና ዘረፋ አጉልቶ አሳይቶናል። ማንም የሕወሃቱን ቁልፍ ሰዎችንና የኤርትራ መሪዎችን ቢያነጻጽር በመሃከላቸው ልዩነት መኖሩን ያስተውላል። ህወሃቶች ሲሰርቁና ሲነውሩ ፐሬዚዴንት ኢሳያስ አፈወርቂና ጓደኞቻቸው ከስርቆትና ነውረኝነት ውጭ ናቸው። ይህ ሁሉ የሠማይ ስባሪ የሚያህል መከራ የተፈራረቀባት ኢትዮጵያ - ማኅህበራዊ መሠረቷ የጋራ እሴቶቿና ማንነትዋ (Social Capital) -ብርቱ ስለሆነ ብቻ ነው እስካሁን ያልጠፋችው።

በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሠላም ለማስፈን የኤርትራ፣ ሶማልያ፣ ኢትዮጵያ ወጣቶች ትብብር

ልበ ሩቅ የሆነችው ሕወሃት - የኤርትራ ነጻ አውጭ ድርጅት ትግልን ተንተርሳ አራት ኪሎ ከደረሰች በኃላ ለሠላሳ ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ መከራ ስታሳጭድ ዳፋው የአፍሪካ ቀንድ ሕዝብንም ጎዳ። ሕወሃት በሕዝብ ትግል ማዕከላዊውን ሥልጣን ተነጥቃ ትግራይ ውስጥ ከመሸገች ሁለት ዓመታት በኃላ መቃብሯን ቆፈረች። በሸንገላ ዳዴ ብላ ሸፍጥ ተመርኩዛ የቆመችው ሸፍታዋ ሕወሃት በዘረፋ ብዛት ሟሟች። መልካምነትና በጎ ፈቃድ ከታከለበት ይህ ነባራዊ ሁኔታ (objective

condition)በአፍሪካ ቀንድ ላይ ዘለቄታዊ ሠላም ለማስፈን ምቹ (favourable)ነው። በአፍሪካ ቀንድ ደሃ ሕዝቦች መካለል አንዳች ቅራኔና ጥላቻ የለም። ኤርትራውያን የሥራ ሰዎችና ታታሪዎች ናቸው። ግልጽነታቸውና ልግስናቸውን በሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ አሁንም አለ። በስደቱ ምክንያት ሶማሊያውያን ከብዙ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ጋር ተግባብተዋል። በርካታ ሱዳን የነበሩ ኤርትራዊና ኢትዮጵያዊ ስደተኞች የሱዳኖቹን ደግነት ያስታውሳሉ። ጅቡታውያንም እንዲሁ ደግ ናቸው። በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ስደትን ንቀው ከሕዝባቸው ጎን ቆመው መከራውን አብረውት የተካፈሉ በርካታ ምሁራን አሉ። የዘመኑን ሌብነትና መሸቀርቀር ንቀው፣ ከእዩኝ ባይነት ይልቅ ትህትናን፣ ከኩራት ይልቅ ደግነትን የሚያስቀድሙየሕዝብ አገልጋዮች በኤርትራ፣ በሁለቱም ሱዳኖች፣ በሶማልያ፣ በጅቡቲና በኢትዮጵያ ውስጥአሉ። እነዚህ ደጎች ሥነ-ምግባርና ግብረገብ ሙሉ ለሙሉ ከአፍሪካ ቀንድ እንዳይጠፉ ሃገራቸውን ጥለው ባለመሰደድ የሚችሉትን አድርገዋል። እነኚህ ብርቱዎች ናቸው የወጣቶቹ አጋዦችና የወደፊቱ ተስፋ ፈንጣቂዎች። በሠባዓዊ ሙብት ጥበቃ ላይ ታትሮ የሚሠራው የሶማልያ ክልል ፕሬዚደንት ወጣቱ ሙስጠፋ ሙሃመድ ኡመር ሕዝቡን አስተባብሮ ሠላም በመፍጠር ደሃውን አላስፈላጊ ከሆነ እልቂት ታግቶታል። ይህን ተምሳሌት ነው የአፍሪካ ቀንዱ ቀጠና ለዘመናት የናፈቀው።

የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ በመነጣጠሉ አልተጠቀመም። ሱዳን በሰሜንና ደቡብ ከተከፈለች በኋላ የደቡብ ሱዳን ሕዝብ ለእርስ በእርስ ጦርነት ሲዳረግ ሰሜኑ ሠላሙ ደፍርሷል። በጎሳዎች ጥንቅንቅ ሳብያ የሶማልያ ሕዝብ እጅግ ተጎድቷል። አምባገነንነትን የታገለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕወሃት መዳፍ ሥር ወድቆ ማቋል። ሕወሃት የዘረጋችው የብልግና ሥርዓት በጎጥ የተሰባሰቡትን ጥቂት ሰዎችና ቤተሰቦቻቸውን አበለጸገ እንጂ ለጅቡቲ፣ ኤርትራ፣ ለሰሜንና ደቡብ ሱዳን፣ ለሶማልያና ኢትዮጵያ ሕዝቦች አንዳች አልፈየደም። የሕወሃት ፍጻሜ ለደጉና ኃይማኖተኛው የትግራይ ሕዝብም ነጻነት ነው።

ወጣቶች አሁን ያለውን ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ለማህበራዊ ዕድገትና እውቀት መስፋፋት ቆርጠው ከተነሱ ለአፍሪካ ቀንድ ሕዝቦች የብሩህ ተስፋ ችቦ ያበሩለታል። ወጣቶች በቅንነት፣ ግልጽነትና ልባዊነት ከተሳሰሩ ስደት ተወግዶ ልማት ይጀመራል። እሺ ግድ የለም ልማት ይቅር፣ ወጣቱ ለቀጠናው ሕዝብ ከተቆረቆረ ሠላም ትሰፍናለች። ሠላም አስተሳሰብን አሳድጋ መግባባቶችን አበርትታ ለውጥ (paradigm shift) ታመጣለች። ድህነት ከጦርነት ጋር ተነባብራ የአፍሪካ ቀንድን ሕዝብ መከራ አብልታዋለች። ድህነት ከሠላም እጦት ጋር የገሃነም ደጀች የሆነችበት የአፍሪካ ቀንድ ሕዝብ "ሁሉ በቀረብኝ" ብሎ "ድህነትን ከሠላም ጋር" ሲመኝ ቆይቷል። ራሳቸውን ከነውረኛነት የጠበቁት ታላላቆቹ የአፍሪካ ቀንድ ምሁራን ልምዳቸውን አካፍለው ወጣቱን እውቀት፣ ክህሎትና ሙያ ካስታጠቁት በቀጠናው ላይ ለውጥ ይመጣል። ቅንነት የተላበሱት ልህቃን መሻቱ ካላቸው የአፍሪካ ቀንድን ከማጥ ያወጧታል። እውነተኛ ምሁራን ብቻ ናቸው የብሽሽቅ፣ የመገዳደል፣ የተረኝነት፣ የዘረፋ፣ ወዘተ፣ ፖለቲካን ከምድሪቱ የሚያስወግዱት። በአፍሪካ ቀንድ ቀጠና ዘለቄታዊ ሠላም በመፍጠሩ ረገድ - ሥልጣንና ኃይል በእጃቸው የያዙት መሪዎች - ማለትም የኤርትራ ፕሬዚደንት ኢሳያስ አፈወርቂ፣ የሶማልያ ፕሬዚደንት ሞሃመድ አብዱላሂ ሞሃመድና የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አህመድ በጎ ፈቃድና ቅንነት ለሠላሙ መስፈን አጋዥ ኃይል ነው።

መደምደምያ

ወጣቶች ልብ ከልብ ከተጣመሩ ስደት ተወግዳ እውቀትትጎለብታለች። ወጣቶች ከተስማሙ ሥነ-ምግባርናግብረገብእቦታቸውተመልሰው ንጽህና፣መጠንን ማወቅ፣ችሮታ፣ጥንቃቄ፣ ደግነትናትህትናይነግሳሉ።ያን ጊዜየአፍሪካ ቀንድ የሠላም ወዳዶች ሃገርትሆናለች።የአፍሪካ ቀንድ የሚደክሙላት፣የሚጠብቋት፣የሚዘምሩላትንቁ ልጆችታገኛለች።እነዚህ ተተኪ ልጆች ናቸው ጥበብ ለብሰው፣ የኃያላን አገሮችን ጣልቃገብነት አለዝበው፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ፍሻሽን ገድበው፣ ፖለቲካንና ትግልን ሠበብ አድርገው የሚያቆራቁሷቸውን ሥልጣን ወዳድ ልህቃን ወጊዱ ብለው የቀጠናቸውን ሠላም በጋራ የሚያስጠብቁት። እማማ አፍሪካም እፎይ ትላለች። በአፍሪካ ቀንድ

ዘላቂ ሠላም ለማስፈን የአፍሪካ ቀንድ ወጣቶች ትብብር የወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ (objective condition) የወለደው አስፈላጊ ሁኔታ (necessary condition) ነው።

እግዚአብሄር በአፍሪካ ቀንድ ላይ ሠላም እንዲሰፍን ይርዳን! አሜን።